# ዘመነ ግርንቢጥ

## ከዓሣዬ

09/05/10

ዶክተሩ ምሁሩ ኸረ ምን ነካቸው
በሃገር ሞት ለመክበር ሆነሣ ሕልማቸው
በ $ 500.አርበኝነት ተመዝግቢ ቢያጡ
የሞኙን ዲያስፖራ ኪሱን ሊያራቁቱ
በአዙሪት ዙረውት እሣት ብለው መጡ
በዘመነ ግርንቢጥ፣
በለመደባቸው ያው፣በነ ክህደት ጌጡ!።

ሌሎቹማ ደግሞ፣
የኣበራሽን ገዳይ እያሽሞነሞኑ
ወግተው ይማር ዓይነት በሥሚ እየማሉ
የ-ያን ትውልድ ሰማዕት እያሞጋገሱ
ትግል የቀጠለውን የአሁኑን ሚያፈራርሱ
ምን ዓይነት ዘመን ነው ዘመነ ግርንቢጥ
በዕምነት ጽናት ቀርቶ፣በክህደት ቅሌት መዝቀጥ ።

በማሰር፣በመግደል ትዝታ ውሥጥ ገብቶ
በደም በጨቀየው ታሪኩ ተኩራርቶ
ኢሰፓው ዶክተሩ በአደባባይ ወጥቶ
ሃቁን ከዶ ዋሽቶ ታሪክ ቀለበሰ
ታጋዩን ኮንኖ ፋሺስት አወደሰ፤
ዘመነ ግርንቢጥ አንት መልከ ዝንጉርጉር
የትግሉ ነው ሕይወቴን ብሎ በመዘመር
ክቡር ሕይወቱን ሰጥቶ የወደቀው ላገር
የኢሕአፓው ጀግና ያ ትውልድ አልነበር!
እኮ ገድሉ ይውጣ! ታሪኩም ይነገር!።

አንጃና ተገንጣይ ባንዳና ፋሺስቱ
ለባዕድ ወግነው ሕዝብን የሚያሥረቱ
አገር ሊያጫርሱ በጠላት ተገዝተው
ጉድ አያልቅባቸው ጉዶች ተሰባሥበው
ብቅ አሉልን ይኸው፣
ጸረ አንድነቱን ሃይል፣
ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ ነው ብለው፣
ሴራው መች አበቃ፣
ውግዝ ከመአሪዮሥ ተብሎ ሃቀኛው
ሲወገዝ ሲወጋ በአገር ምንደኛው
አይ ዘመነ ግርንቢጥ፣
የታሪክ አተላን ፈልፋይ በየሙጃው ።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.